## መግቢያ

የዛሬው የኢትዮጵያ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት አገልግሎት “የሕዝብ ቤተመጻሕፍት ወመዘክር” በሚል ስያሜ በ1936 ዓ.ም በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ተመርቆ የተከፈተ ሲሆን፤አገልግሎት መስጠት የጀመረውም ንጉሱ ባበረከቱት የመጻሕፍት ስጦታ ነው፡፡

በአሁኑ ወቅትም የሪከርድ ሥራ አመራርና የመረጃ ሥርዓት በመዘርጋት መዛግብትን፣ የጽሑፍ ቅርሶችን፣ የታተሙ እና ያልታተሙ የመረጃ ውጤቶችን በማሰባሰብ፣ በማደራጀት፣ በመጠበቅ፣ ተደራሽ በማድረግና የጥናትና ምርምር ሥራን በማሳደግ ለትውልድ ማስተላለፍ እንዲሁም የእውቀትና የክህሎት ማሳደጊያና የልዕቀት ማዕከል በመሆን በእውቀት የበለፀገ ማህበረሰብ መፍጠርን ተልዕኮው አድርጎ እየሰራ ይገኛል፡፡





## ሰነዶችን መጠበቅ ያለው ጠቀሜታ

- ሰነዶች የተቋማትንና የማህበረሰብን የለት ተለት እንቅስቃሴ መዝግበው በመያዛቸው፣
- ለ ጥናትና ምርምር፣ ፖሊሲ ለማርቀቅ ግብዓት በመሆናቸው፣
- ለሚደረጉ የስርዓት መሻሻሎች እንዲሁም ውሳኔዎች መስፈንጠርያ መደላድል በመሆናቸው፣
- ካለፈው ተነስቶ እስከ ሚቀጥለው የትውልድ ሰንሰለት የሚተላለፉ ሀብት በመሆናቸውና ከዚህም ለላቀ ፋይዳቸው ተገቢ ጥበቃና እንክብካቤ ያሻቸዋል፡፡



## ሰነዶችን ማዛወር፡ ቁልፍ ሂደት (Record Acquisition: A Vital Process)

የኢ/ቤ/ቤ/አ ብሔራዊ የሰነድና መዛግብት ቋትን ለማበልጸግ እንዲሁም አግባብነት ባለው መልኩ ህግና ሙያውን የጠበቀ የሰነድ ቅብብሎሽ እንዲኖር ከአመንጪ ተቋማት ጋር የሚደረገው ትብብር አስፈላጊ እንደሆነ ያምናል፡፡

ለዚህም ተቋሙ በአዋጅ ቁጥር 179/91 በሀገሪቱ የሚገኙ መዛግብትን፣ መጻሕፍትንና መሠል ጽሑፎችን በአንድ ማዕከል ስር በማሰባሰብና በማደራጀት የሀገሪቱን የመረጃ አገልግሎት በተቀናጀ ሁኔታ መምራት የሚያስችለውን ህጋዊ ሰውነት አግኝቷል፡፡

## የሰነዶች ምዘና፣ መረጣ እና ውገዳ ምንድነው?
## (Records appraisal and disposal)

የሰነዶች ምዘና፣ መረጣና ውገዳ በሰነድና መዛግብት አስተዳደር ስርዓት ውስጥ ሰነዶች የአገልግሎት ጊዜያቸውና ይዘታቸው የሚወሰንበት፣ የአገልግሎት ጊዜያቸውን የጨረሱና ዘላቂ ጠቀሜታ ያላቸው ሰነዶች አስፈላጊው ጥናትና ግምገማ ተደርጎባቸው በመዛግብትነት የሚጠበቁበት፣ ዘላቂ ጠቀሜታ የሌላቸው ደግሞ ህግና መመርያውን ተከትለው የሚወገዱበት ሙያዊ ተግባር ነው፡፡

## የሰነዶች ምዘና፣ መረጣ እና ውገዳ በተቋማችን

በተቋማችን ይህ ተግባርና ሀላፊነት ከተሰጠው ጊዜ ጀምሮ ከአመንጪ ተቋማትና ግለሰቦች የአገልግሎት ጊዜያቸውን የጨረሱ ሰነዶችን በማዛወርና ጠብቆ በማቆየት መዛግብት ሊሆኑ የማይችሉ ሰነዶችን ደግሞ በአስተማማኝና ደህንነቱን በጠበቀ መልኩ በማስወገድ ላይ ይገኛል፡፡












## አመንጪ ተቋማት የሚያገኙት ጠቀሜታ



አመንጪ ተቋማት የአገልግሎት ጊዜያቸውን የጨረሱ ሰነዶችን በማዛወራቸው

- በሰነዶቹ ላይ ያለ ዘርፈ ብዙ ስጋቶችን በመቀነስ፣
- የሰነድ አስተዳደር ሸክምን በማቃለል፣
- የአገልግሎት ቅልጥፍናን በማዳበር፣
- የቦታና በጀት ቁጠባ፣
- የሀገር የመረጃ ሀብትን በማበልጸግ እና ለትውልድ በማስተላለፍ፣
- ለጥናትና ምርምር አስተዋጽኦ በማበርከት ረገድ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

## መደምደሚያ

የኢትዮጵያ ቤተ-መዛግብትና ቤተ-መጻሕፍት አገልግሎት ከሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት መካከል የሰነዶች ምዘና፣ መረጣና ውገዳ አንዱ ነው፡፡ ይህንንም ከመቼውም ጊዜ በላይ በስፋት ለማከናወን የተነሳበት ጊዜ ለመሆኑ በ2016 ዓ.ም ተመርቆ ስራ የጀመረው የመዛግብት ህንፃ እና በትብብር እየሰሩ ያሉ በርካታ ተቋማት ምስክሮች ናቸው፡፡

### አድራሻ

Website www.nala.gov.et
Email nala@ethionet.et
Fax 0115 52 64 11
P.O.Box 717

0115 15 0882

Ethiopian Archive and Library Agency

የኢትዮጵያ ቤተ-መዛግብትና ቤተ-መጻሕፍት አገልግሎት
https://t.me/wamezeker